# የጤና መድህን/ኢንሹራንስ ተደራሽነትን ለሁሉም ማስፋት
## (ሕጋዊ ወረቀት የሌላቸውን ሰደተኞችን ጨምሮ)

በዚህ ጥቅምት-ህዳር (በኖቬምበር) ወር ጀምሮ በዋሽንግተን ግዛት የሚኖር ማንኛውም ሰው የኢሚግሬሽን ሁኔታው ምንም ይሁን ምን Washington Healthplanfinder (በዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር) በኩል የጤና እና የጥርስ ኢንሹራንስ የመግዛት እድል ይኖረዋል።

ታህሳስ 22 ቀን 2016 ዓ.ም (ጃንዋሪ 1ቀን 2024) ለሚጀመረው የጤና ሽፋን እስከ ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም (ዲሴምበር 15) ይመዝገቡ።

washington healthplanfinder
click. compare. covered.

### ቊልፍ ቃላት

**ፕሪሚየም/ወርሃዊ ክፍያ፦** እያንዳንዱ አባል ፕሪሚየም የሚባል ወርኀዊ ክፍያ ይከፍላል። የፕሪሚየም ዋጋዎ በጤና መድን/ኢንሹራንስ ዕቅድዎ ላይ የተመሰረተ ነው።

**የተቀናሽ ክፍያ ግዴታ፦** የጤና መድንዎ/ኢንሹራንስዎ ሂሳቦችዎን ለመክፈል መርዳት የሚጀምረው "ተቀናሽ የሚሆነውን" መጠን ካሟሉ በኋላ ነው። ሁሉም እቅዶች የመከላከያ እንክብካቤን የሚከፍሉት ተቀናሽዎ ከመሟላቱ በፊት ነው። የካስኬድ እንክብካቤ (ካስኬድ ኬር) እቅዶች ተቀናሽዎ ከመሟላቱ በፊት ለበለጡ አገልግሎቶች ይከፍላሉ። እነዚህ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የመከላከያ እንክብካቤ
- ለበሽታ ወይም ለጉዳት ህክምና መደበኛ የህክምና ሐኪም ለማየት
- የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶች
- አጠቃላይ የመድሃኒት ማዘዣዎች
- አስቸኳይ እንክብካቤ፣ ወዲያውኑ እንክብካቤ ሲያስፈልግዎ ግን እንደ የልብ ድካም ያለ ድንገተኛ ሁኔታ በማይኖርበት ጊዜ።

**የጋራ ክፍያ እና የጋራ መድን፦** እነዚህ ወደ ሐኪም ሲሄዱ የሚከፍሏቸው ወጪዎች ናቸው። የጋራ ክፍያዎ ቋሚ መጠን ($1-$50)ያለ ነው። የጋራ መድንዎ የአገልግሎት ወጪ በመቶኛ ነው። የጤና መድንዎ ለቀሪ ቀጠርዎ ይከፍላል።

## ብቁነት፣ የኢሚግሬሽን ሁኔታ እና ደኅንነት

### ማን ብቁ ነው?

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ሕጋዊ ሰነድ የሌለው ሰደተኛ ቢሆኑም እንኳን በ*Washington Healthplanfinder* (በዋሽንግተን ሄልዝፕላን ፋይንደር በኩል) የጤና መድን/ኢንሹራንስ መግዛት ይችላሉ፤ ። የአሜሪካ ዜግነት፣ ግሪን ካርድ ወይም ሌሎች የኢሚግሬሽን ወረቀቶች አያስፈልጉዎትም።

### የጤና መድን ማግኘቴ በኢሚግሬሽን ሁኔታዬ ወይም በዜግነት ማመልከቻዬ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል?

የጤና መድን ማግኘቴ በእርስዎ፣ በቤተሰብዎ ወይም ከእርስዎ ጋር አብሮ በሚኖር ማንኛውም ሰው የኢሚግሬሽን ሁኔታ ወይም የዜግነት ማመልከቻ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።

### የጤና መድን ማግኘቴ" የሕዝብ ሸክም" ያደርገኛል?

የጤና ኢንሹራንስ ማመልከቻ ማቅረብ ወይም መቀበል እና ለኢንሹራንስ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ መቀበል አንድን ሰው" የህዝብ ሸክም" አያደርገውም። ይህ ማለት ለእርስዎ፣ ለቤተሰብዎ ወይም ከእርስዎ ጋር ለሚኖር ማንኛውም ሰው የኢሚግሬሽን ሁኔታ ወይም የዜግነት ማመልከቻዎች ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም።

### እኔ ሕጋዊ ሰነድ የለኝም መረጃዬ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው?

ደህንነትዎ ለእኛ አስፈላጊ ነው። መረጃዎ ለኢሚግሬሽን አፈጻጸም ጥቅም ላይ አይውልም።

የፌዴራል እና የክልል ህጎች በዋሽንግተን የጤና እቅድ ፈላጊ *Washington Healthplanfinder* በኩል የጤና መድን/ኢንሹራንስ ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎችን ግላዊነት ይከላከላሉ። የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው ለሽፋን ብቁነትን ለመወሰን እንጂ ለኢሚግሬሽን አፈጻጸም አይደለም።

# ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ምዝገባ

### “ምዝገባ” ምንድን ነው?

*Washington Healthplanfinder*(በዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር) የጤና እቅድ ፈላጊ በኩል የጤና እቅድ በመምረጥ እና ከዚያ ለጤና ዕቅድዎ በመክፈል በጤና መድን/ኢንሹራንስ ውስጥ ይመዘገባሉ።

### መቼ ነው መመዝገብ የምችለው? “ክፍት ምዝገባ” ምንድን ነው?

ማንኛውም ሰው *Washington Healthplanfinder,* (በዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር) በኩል ከጥቅምት 21 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥር 6 ቀን 2016 ዓ.ም (ከኖቬምበር 1 እስከ ጃንዋሪ 15) ባለው ጊዜ ውስጥ ለጤና መድን/ኢንሹራንስ መመዝገብ ይችላል። ይህ ጊዜ ክፍት የምዝገባ ጊዜ ይባላል። ክፍት ምዝገባ በየዓመቱ ይካሄዳል።

### ክፍት ምዝገባ ቢያመልጠኝስ?” ልዩ ምዝገባ” ምንድን ነው?

አንዳንድ ሰዎች በሌሎች ጊዜያት መመዝገብ ይችላሉ። ይህ ልዩ ምዝገባ ይባላል። በሕይወትዎ ውስጥ ለውጥ ካጋጠምዎት( ሥራ ማጣት፣ የጋብቻ ሁኔታ ለውጥ፣ ልጅ መወለድ፣ ወዘተ) ወይም ዝቅተኛ ገቢ ካለዎት፣ ከክፍት ምዝገባ ምዝገባ ውጭ መመዝገብ ይችሉ ይሆናል።

### ለመመዝገብ ምን ያስፈልገኛል?

ብቁ መሆንዎን ለመወሰን *Washington Healthplanfinder* (ዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር) ስለእርስዎ እና ስለ ቤተሰብዎ መረጃ ይጠይቃል

### ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

ማመልከቻው 1 ሰዓት ያህል ሊወስድ ይችላል.

### ለመመዝገብ እርዳታ ማግኘት የምችለው ከየት ነው? በሌሎች ቋንቋዎች እርዳታ ይገኛል?

ሁሉም የምዝገባ እርዳታ ነጻ ነው*እዚህ ላይ እርዳታ ለማግኘት እነዚህ ሦስት መንገዶች አሉ፦

**ይደውሉ**

**በስልክ ፦ 1-855-923-4633**
**ቲቲዋይ/ቲዲዲ ፦ 1-855-627-9604**

እርዳታ ከ200 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ይገኛል።

**ይገናኙ**

በህብረተሰብዎ ውስጥ ከሚገኝ የጤና አሳሽ፣ ደላላ ወይም የታመነ ግብዓትጋር ቀጠሮ ይያዙ።

**ይመልከቱ**

wahealthplanfinder.org

የኪውአር(QR) ኮድ ይቃኙን

[ፍንጭ] በአካባቢያችሁ የሚገኙ የጤና እቅዶችን አስቀድማችሁ ለማየት wahealthplanfinder.org. (ዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር) የሚለውን ድረ ገጽ በመጎብኘት” የጤና እቅዶችን ፈልግና አወዳድር” የሚለውን መክፈቻ ቁልፍ በመጫን ተጠቀሙ።

*አንድ ሰው እርሰዎን ለመርዳት ማረጋገጫ ያለው ካላወቁ ወይም ለአገልግሎታቸው ክፍያ እንዲከፈላቸው ከጠየቁ፣ ለ*Washington Healthplanfinder* (ለዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር) የደንበኛ ድጋፍ ማዕከል በስልክ ቁጥር 1-855-923-4633 ይደውሉ።



# ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የጤና መድን/ኢንሹራንስ ዋጋ

### የጤና ኢንሹራንስ ዋጋ ምን ያህል ነው?

የጤና ኢንሹራንስ የመግዛት ዋጋ እንደ ገቢዎ፣ የቤተሰብዎ መጠን እና የት እንደሚኖሩ ባሉ ነገሮች ላይ የተመሰረተ ነው።

wahealthplanfinder.org ላይ እቅዶችን ያሰሱ እና ያወዳድሩ ወይም አንድ እቅድ ምን ያህል እንደሚያስከፍልዎ ለማወቅ በማህበረሰብዎ ውስጥ ካለው የታመነ ግብዓት ጋር ይሥሩ።

### እነዚህ ቃላቶች፦ ፕሪሚየም/ወርሃዊ ክፍያ ፣ ተቀናሽ ክፍያ ግዴታ፣፣ የጋራ መድን/ኢንሹራንስ፣ እና የጋራ ክፍያ ማለት ምን ማለት ናቸው?

> **ፕሪሚየም/ወርሃዊ ክፍያ፦** እያንዳንዱ አባል ፕሪሚየም የሚባል ወርኀዊ ክፍያ ይከፍላል። የፕሪሚየም ዋጋዎ በጤና መድን/ኤንሹራንስ ዕቅድዎ ላይ የተመሰረተ ነው።
>
> **የተቀናሽ ክፍያ ግዴታ፦** የጤና መድንዎ/ኢንሹራንስዎ ሂሳቦችዎን ለመክፈል መርዳት የሚጀምረው “ተቀናሽ የሚሆነውን” መጠን ካሟሉ በኋላ ነው። ሁሉም ዕቅዶች ተቀናሽ ክፍያው ከመጠናቀቁ በፊት ለተወሰኑ ነገሮች ለምሳሌ ለጤና ምርመራዎች ይከፍላሉ።
>
> **የጋራ ክፍያ እና የጋራ መድን፦** እነዚህ ወደ ሐኪም ሲሄዱ የሚከፍሏቸው ወጪዎች ናቸው። የጋራ ክፍያዎ ቋሚ መጠን ($1-$50)ያለ ነው። የጋራ መድንዎ የአገልግሎት ወጪ በመቶኛ ነው። የጤና መድንዎ ለቀሪ ቀጠርዎ ይከፍላል።

### “ከኪስዎ የሚወጡ” ወጪዎች ምንድን ናቸው?

ከኪስዎ የሚወጡ ወጪዎች( ፕሪሚየም/ወርሃዊ ክፍያ ፣ ተቀናሽ ክፍያ ግዴታ፣ የጋራ መድን/ኢንሹራንስ፣ እና የጋራ ክፍያ) ወደ ሐኪም ሲሄዱ የሚከፍሉትን ገንዘብ ያመለክታሉ።

## እቅድ መምረጥ

### የትኞቹ የጤና መድን/ኢንሹራስ እቅዶች ይገኛሉ?

በ *Washington Healthplanfinder* (በዋሽንግተን ሄልዝፕላንፋይንደር)በኩል ባለሦስት ደረጃ የጤና መድን/ኢንሹራንስ እቅዶች ይገኛሉ፦ የነሐስ፣ የብር እና የወርቅ።

የጤና ኢንሹራንስ ኩባንያዎ የሚከፍለው መጠን እርስዎ በመረጡት ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነው። የነሐስ እቅድ 60% ገደማ ይከፍላል፣ የብር እቅድ 70% ገደማ ይከፍላል፣ እና የወርቅ እቅድ 80% ገደማ የህክምና ሂሳቦችዎን ይከፍላል።

> **ነሐስ፦** እነዚህ እቅዶች በወር ያነሰ ያስከፍላሉ ነገር ግን እንክብካቤ በሚፈልጉበት ጊዜ አነስተኛ ወጪ ይከፍላሉ።
>
> **ብር፦** እነዚህ  እቅዶች እንክብካቤ በሚፈልጉበት ጊዜ ተጨማሪ ወጪዎችዎን ይሸፍናሉ ነገር ግን የበለጠ ዋጋ ሊያስከፍሉ ይችላሉ። ለካስኬድ እንክብካቤ ቁጠባ (ካስኬድ ኬር ሴቪንግ) ብቁ ከሆኑ እነዚህ እቅዶች ከነሐስ እቅዶች ያነሰ ዋጋ ሊያስከፍሉ ይችላሉ።
>
> **ወርቅ፦** እነዚህ እቅዶች በወር የበለጠ ዋጋ ያስከፍላሉ ነገር ግን እንክብካቤ በሚፈልጉበት ጊዜ የበለጠ ወጪዎችን ይከፍላሉ። ለካስኬድ እንክብካቤ ቁጠባ (ካስኬድ ኬር ሴቪንግ) ብቁ ከሆኑ እና ከፍተኛ የጤና እንክብካቤ ፍላጐቶች ካሉዎት እነዚህ እቅዶች ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

### የብር ወይም የወርቅ እቅድን ከመረጥኩ የተሻሉ ዶክተሮችን አገኛለሁን?

አይ- የእንክብካቤው ጥራት ለሁሉም እቅዶች ተመሳሳይ ነው።

washington healthplanfinder
click. compare. covered.

[ጥቆማ] የካስኬድ እንክብካቤ (ካስኬድ ኬር) ዓርማውን   ይፈልጉ። እነዚህ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው እቅዶች ዋጋቸው አነስተኛ ነው እና ወርኀዊ ወጪዎን( ፕሪሚየም) ለመቀነስ የግዛቱን (የስቴት) ቁጠባዎችን ማግኘት ይችሉ ይሆናል።

CASCADE CARE